# የደቀ መዝሙር ሕይወት የራሱ አይደለም
# A Disciple's Life Is Not His Own
ሪክ ጆይነር Rick Joyner

ጆሮቻቸው እንዲኮረኮሩ ብቻ ስለሚፈልጉ ብዙዎች በመጨረሻው ዘመን እንደሚታለሉ ሐዋርያው ጳውሎስ አስጠንቅቆአል፥ ማለትም አስቸጋሪ ወይም የሚፈትን አንዳች መስማትን ሊታገሱ አይችሉም። ለሳምንቱ ከሆነው ቃል ጋር ለሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታት ብትቀጥሉ፥ እናንተ በዚያ ክፍል(ከላይ በተጠቀሰው ምድብ) ውስጥ እንዳልሆናችሁ እናውቃለን፥ ምክንያቱም በመጀመሪያ ስለ ደቀመዝሙርነት እጅግ በጣም አስቸጋሪ የሆኑትን ጠቃሚ ጉዳዮች እየተናገርን ስለሆነ፥ ጌታ በሉቃስ 14፥33 እንደተናገረው:

**"እንግዲህ እንደዚሁ ማንም ከእናንተ ያለውን ሁሉ የማይተው ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።"**

ምናልባት ቃል በቃል ሊሆን ይችላል? ይህ ቃል በቃል ነው። ጌታ ሀብታሙን ወጣት ገዢ እንዳዘዘው(ከሀብታሙ ወጣት ገዢ እንደጠበቀው) ጌታን ለመከተል ያለንን ሁሉ የግድ መሸጥና ለድሆች መስጠት አለብን ማለት ነው? የግድ አይደለም። ያ ማለት እኛ ሕይወታችንን ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስንሰጥ እኛ ያለን (የእኛ የሆነው) ሁሉ የእርሱ(የጌታ) ይሆናል ማለት ነው። እኛ በዋጋ ተገዝተናል፥ ከእንግዲህም ለራሳችን አይደለንም ነገር ግን ለእርሱ(ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ) ነን።

የጌታ ደቀመዝሙር ስንሆን፥ በራሳችን ህይወት(ኑሮ) ቁጥጥር ውስጥ ከመሆን ወደ ጌታ ሥልጣን ስር እንሄዳለን። ከሰው ጋር ሳይሆን ከዩኒቨርሱ(ሁሉን ፍጥረታት ከፈጠረው) ጌታ ጋር ነው እያወሳን(እየተግባባን) ያለነው። እግዚአብሔርን አለመታዘዝና ያለ እርሱ ዓለምን ማንቀሳቀስ እችላለሁ ከሚል የሰው አስተሳሰብ ውጤት የተነሣ ነው እያንዳንዱ ችግር የመጣው። ለእያንዳንዱ የሰው ችግር መልሱ ወደ እግዚአብሔር መመለስና በሁሉም ነገሮች እግዚአብሔርን ለመታዘዝ መፈለግ ነው። እኛ ያለን ሁሉ ከእንግዲህ የእኛ እንዳልሆነ ነገር ግን የእግዚአብሔር እንደሆነ ድረስ መታዘዝ ነው፥ እኛም አስተናጋጆቹ ብቻ (just stewards) ነን። እግዚአብሔር ሁሉን እንድንሰጥ ይጠይቀን ወይም እኛ ያለንን መምራት የእርሱ ኀላፊነት ነው፥ ይህ ግን ለእኛ ፍጹም ነፃነት ብቸኛው መንገድ ነው።

ይህ እጅግ በጣም የከበረውን የእኛን ንብረት፣ ጊዜያችንን ያካትታል። ከእንግዲህ ለራሳችን አንኖርም ነገር ግን በሁሉም መልኩ ለእርሱ(ለእግዚአብሔር) እንኖራለን። በቃ የፈለግነውን አናደርግም፥ ነገር ግን በሁሉም ነገሮች የእርሱን ፈቃድ እንፈልጋለን።

እንደ አገልጋዮች ስንበስል፥ የበለጠ ነጻነትና የበለጠ ሥልጣን ይሰጠናል። ታማኝ አገልጋዮች እርሱ(እግዚአብሔር) ሁሉንም ነገሮች የሚያካፍላቸው(የሚነግራቸው) የእርሱ ጓደኞች ይሆናሉ። ታማኝ ጓደኞች እግዚአብሔር ማንኛውም ሰው ንጉሥ ሊለማመደው ከሚችለው እጅግ በላይ ነጻነትንና ሥልጣንን ጨምሮ ሁሉንም ነገሮች የሚሰጣቸው የእርሱ ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆች መሆን ይችላሉ። ነገር ግን፥ መሠረታዊ ከሆነ ፍጹም ጥልቅ(በጣም ታላቅ) መታዘዝ ይጀምራል።

የእውነተኛ ደቀመዝሙር ህይወት (ኑሮ) እኛ በአንዳንድ መንገዶች(መልኮች) ልንኖረው የምንችለው እጅግ በጣም አስቸጋሪው ኑሮ ነው፥ ነገር ግን ደግሞ እጅግ በጣም ነጻ አውጪ፣ የሚሣካ(የሚፈጸም)፣ እና አስደሳች ነው። ልናውቀው የምንችለው እጅግ ታላቁ ነጻነት የክርስቶስ ባሪያ መሆን ነው። ቀላል አይደለም፥ ነገር ግን በዚህ ህይወት በሁሉም መልኩ የተገባው ነው፥ ከዚያም የዘላለም ሕይወት ፍጹም ጥቅም አለን።

የእውነት በዚህ መንገድ የሚኖር ግን ማን ነው? እውነተኛ ደቀ መዝሙሮች ያደርጉታል። ብዙ ደቀ መዛሙርት የሉም፥ ነገር ግን አንዳንዶች አሉ። እየገባንባቸው ያሉት ጊዜያት እውነተኛ ደቀ መዝሙሮችን ከአስመሳዮቹ ይገልጻሉ(ያሳያሉ)። ሊመጣ ያለውን ቁጣ ለማምለጥ በእርሱ ማመን ብቻ በቂ ነው ብለው በማሰብ "የእሳት አደጋ ኢንሹራንስ፥" ብቻ የሚፈልጉ፥ ነገር ግን እርሱ ያለውን የእውነት የማያደርጉ፥ የእርሱ ፈቃድ ምን እንደሆነ ለማወቅ መፈለግ እንኳ በበቂ ሁኔታ የማያስቡ፥ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ መሠረት እጅግ በጣም አሳዛኝ ፍጻሜ ሊኖራቸው ነው።

ለማንኛውም ግንኙነት ታላቁ ውርደት ግዴለሽነት(ችላ ማለት) ነው። ጌታ በራእይ 3፥16 ለብ ያሉትን ከአፉ እንደሚተፋ ተናግሮአል። እግዚአብሔር መልካም(ደግ) እና ታጋሽ(ትእግስተኛ) ነው፥ ነገር ግን ለትእግስቱ ልክ እንዳለው እርሱ በጣም ግልፅ አድርጎታል፥ እርሱም በጥርጣሬ የምንወስደው አይደለም። የእርሱ ተከታይ ነን በማለት ጌታን መጥራት እና በስሙም መጠራት እጅግ በጣም ትኩረት(ጥንቃቄ) ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። እርሱ ስለዚህ በማቴዎስ 7፥21-23 አስጠንቅቆአል:

**"በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።"**

**"በዚያ ቀን ብዙዎች። ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል።"**

**"የዚያን ጊዜም። ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።"**

እዚህ ጋር "ብዙዎች" በዚያ ቀን በጣም ያልተለመዱ (ልዩ) ሥራዎች በስሙ አድርገው ወደ እርሱ እንደሚመጡ እናያለን ነገር ግን መንግሥተ ሰማይ መግባት አይችሉም! ጌታ ሳይቀበላቸው የሚቀሩትን እነዚህን "አላወቃቸውም" (did not "know") የሚለው ቃል እነርሱ ማን እንደሆኑ ለማወቅ ከተጠቀመበት ቃል ጋር አንድ አይደለም። እዚህ ጋር ጥቅም ላይ የዋለው "አወቀ" የሚለው ቃል ባልና ሚስት እንዳላቸው ጥልቅና እጅግ የተቀራረበ ግንኙነት ነው። [እግዚአብሔር አምላክ ጌታችን ክርስቶስ ኢየሱስ ከፈጠረው ሰው ጋር መንፈስ ለመንፈስ ልብ ለልብ አሳብ ለአሳብ ፈቃድ ለፈቃድ ጥልቅ ኅብረት ግንኙነት ይፈልጋል። አዳም ከመውደቁ በፊት በገነት መንግሥተ ሰማይ እንደነበረው ዓይነት። ያንን ኅብረት ለማደስ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ በአባቱ በእግዚአብሔር አብና በፍጡራኑ በሰዎች መካከል አስታራቂ ማላጅ በመሆን በቀራንዮ መስቀል ላይ ደሙን አፍስሶ፣ ሞቶ፣ ከሞትም በሦስተኛው ቀን በእግዚአብሔር መንፈስ ተነሥቶ በአርባኛውም ቀን ወደ አባቱ እግዚአብሔር አብ አርጎ በአባቱ ቀኝም በክብር በኃይል በፍቅር በበረከት ተቀምጦ ያ ግንኙነት ኅብረት በእርሱ ለሚያምኑና እንደ አባቱ ፈቃድ ቃሉን እያደረጉ ለሚኖሩ ሁሉ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል እንዲቀጥል ያደረገው ለማለት ነው። ጌታችንና ሕይወታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያሑሹዋ ሐማሺያክ በእርሱ

አምነን እንደቃሉ የምንኖረውን ወደ ቅዱስ መንግሥቱ እርሱ ባለበት እኛም እንሆን ዘንድ ሊወስደን ዳግም ይመጣል፤ ያንንም ኅብረት እለት እለት ከክርስቶስ ኢየሱስ ከሊቀ ካህናችንና መድኃኒታችን ጋር ከመንፈስ ቅዱስም ጋር በመሆን በየጊዜው ከእርሱ ጋር በቅድስና በጽድቅ እንደቃሉ በንጽህና መኖር አለብን ሲል ነው። ሃሌ ሉያ። ክብር ለጌታ ክብር ለነገሥታት ንጉሥ ለጌታ ለናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ] **እግዚአብሔር** ሰውን የፈጠረው ለዚህ ዓይነቱ ኅብረት ግንኙነት ነው፥ እናም አጥብቀን ልንሠራቸው ከምንችላቸው ሌሎች ሥራዎች ውጪ ከ**እግዚአብሔር** ጋር ይህን ኅብረት በመያዝ ብቻ ነው የእውነት ስኬታማ ህይወት ያለመቋረጥ ማሳካት የምንችለው።

ከ**እግዚአብሔር** ጋር ይህን ኅብረት ለመያዝ(ለማግኘት) አሁንም ጊዜ አለ። ይህ በፍጥረታት ሁሉ እጅግ በጣም ታላቁ እድል ነው። አትጣሉት አታባክኑት።

**ክብር፥ ኃይል፥ በረከት፥ ምስጋና፥ ጥበብ፥ ማዳን፥ ቅድስና፥ ውዳሴ፥ አምልኮ እጅግ በከበረ ቡሩክ ዙፋኑ ላይ ላለ የእስራኤል ኃያል አምላክ የሠራዊት ጌታ፥ አንድ አምላክ ለሆነ ለእግዚአብሔር አብ ለወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመንፈስ ቅዱስ ይሁን አሜን። ማራናታ ጌታ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የአብ ቃል**

ሊያደርግ የሚገባውን ያደረገ፥ የማይጠቅም ባሪያ ተረጎመው። **ሃሌ ሉያ**

http://www.shekinahworship.com/

https://www.youtube.com/user/angeltvsss

https://www.divinerevelations.info/amharic